


# ለ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማመልከት

## የትምህርት ዓመት 2026-27

ዲስትሪክቱ ለ70 የህዝብ እና የህዝብ ቻርተር መካከለኛ ትምህርት ቤቶች/የትምህርት ካምፓሶች መኖሪያ ነው። ተማሪዎች በ My School DC ማመልከቻ ላይ እስከ 12 መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማመልከት ይችላሉ። እንዲሁም በቀጥታ በ DCPS የአካባቢ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ መጋቢ ትምህርት ቤት፣ ወይም በ My School DC ውስጥ ለማይሳተፍ ትምህርት ቤት የማመልከት አማራጭ አላቸው።

### እስከ ማርች 2፣ 2026 ድረስ ያመልክቱ

- **የቤተሰብ መለያ ያዘጋጁ።**
  ለተማሪዎች ጠቃሚ ምክር:- በግል የኢሜይል አድራሻዎ የቤተሰብ መለያ ከፈጠሩ፣ በማመልከቻው ደረጃ 2 ላይ የአሳዳጊዎን ኢሜይል አድራሻ ማካተትዎን ያረጋግጡ።
- **የMy School DC ማመልከቻዎን ለመሙላት የሚፈልጉትን መረጃ ሁሉ ይሰብስቡ።**
  ሁሉም የሚያስፈልጉት መረጃዎች ከሌሉዎት ማመልከቻውን ማስገባት አይችሉም። የዚህን መረጃ ማስፈንጠሪያ ለማግኘት የQR ኮዱን ይቃኙ።
- **በMy School DC ማመልከቻዎ ላይ ትምህርት ቤቶችን ያክሉ እና እርስዎ በሚፈልጉት ቅደም ተከተል ደረጃ ይስጧቸው።**
  ትምህርት ቤቶችዎን ደረጃ የሰጡበት ቅደም ተከተል ከትምህርት ቤቶች ጋር ሲዛመዱ የፈለጉበትን ቅደም ተከተል እንድናውቅ ያስችለናል፤ እንደ ወንድም እና እህት ወይም የዝውውር ምርጫዎች ላይ ብቁ መሆን ያሉ ማንኛውንም ምርጫዎች አይነካም።
- **ማመልከቻዎን እስከ ማርች 2 ድረስ ያስገቡ።**
  በማመልከቻዎ ላይ ከማርች 2 በፊት በማንኛውም ጊዜ ማረም ይችላሉ። የእርስዎን የትምህርት ቤት ደረጃዎች ። እስከ ማርች 13 በ 5 p.m. ድረስ ማዘመን ይችላሉ።

### ከማመልከትዎ በፊት

- **ዝርዝር ያዉጡ።**
  School Finder (http://find.myschooldc.org) ተጠቅመው ትምህርት ቤቶችን በአድራሻ፣ በክፍል እና በፕሮግራም አይነት ይፈልጉ። እንዲሁም በዚህ መሳሪያ ወደ ትምህርት ቤት የመጓዝ እድልዎን ማሳየት ይችላሉ። ማስታወሻ:- በተመለከቷቸው ትምህርት ቤቶች የእጣ ውድድር ወይም የመጠበቂያ ዝርዝር አቅርቦት ላይ ምንም አይነት ዋስትና ስለሌለ ሊከታተሏቸው በሚፈልጉት ሚፈልጓቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ ያመልክቱ። እስከ 12 ማመልከት ይችላሉ!
- **የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት መለያን ይመልከቱ።**
  የትምህርት ቤት መለያዎች ስለ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት መሰረታዊ መረጃን ያሳያሉ እናም እርስዎ የክፍት ቤት መርሃ ግብራቸውን ማየት ይችላሉ። ማመልከቻዎች* የሚወስዱበትን ውጤቶች፣ እንዲሁም በአንድ ክፍል የሚገኙ የመቀመጫዎች ቁጥር ያለፉ የእጣ መረጃዎችን ብዛት፣ በውጤት ጊዜ የተጠባባቂ ዝርዝሩን ርዝመት እና የመጠበቂያ ዝርዝር እንቅስቃሴን የሚያሳይ ማስታወሻ ይያዙ። የዚህን መረጃ ማስፈንጠሪያ ለማግኘት የQR ኮዱን ይቃኙ።
- **EdFEST፣ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች፣ እና ክፍት ቤቶች ላይ ይሳተፉ።**
  ምርጫዎችዎን ለማጥበብ እንዲረዱዎት በቀጥታ ለሚፈልጓቸው ትምህርት ቤቶች ጥያቄዎችን ይጠይቁ።

*ጠቃሚ:- አብዛኛው መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚጀመሩት 4ኛ ወይም 5ኛ ክፍል ላይ ነው። ይህ ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት መቼ እንደሚያመለክቱ ሲወስኑ ማወቅ ያለብዎት ነገር ነው።

- **አውታረ መረቦችዎን ይጠቀሙ።**
  እርስዎ ስለሚያመለክቱባቸው ትምህርት ቤቶች እውቀት ካላቸው ሰዎች (ለምሳሌ፦ ጎረቤቶች፣ ጓደኞች፣ የትምህርት ቤት አማካሪዎች) ጋር መነጋገር ጠቃሚ ነገር ነው።
- **የደረጃ አሰጣጥዎን ይወስኑ።**
  የመጨረሻውን የትምህርት ቤቶች ዝርዝርዎን እርስዎ በመረጡት ቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ። ዝርዝርዎን በዚህ ቅደም ተከተል ደረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው። የእርስዎ ተዛማጅ ትምህርት ቤት ከላይ ባስቀመጡት ትምህርት ቤቶች የተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ብቻ ያገኛሉ።

**በወረቀት ላይ ማንበብ ይፈልጋሉ? ሁሉንም የተጠቀሱ ማስፈንጠሪያ ዎች ለማግኘት እዚህ ይቃኙ**

## የህዝብ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አይነቶች

- **DCPS የአካባቢ ትምህርት ቤቶች**፦ የMy School DC ማመልከቻ አስፈላጊ **አይደለም**።
- **DCPS እና የቻርተር መጋቢ ትምህርት ቤቶች**፦ የMy School DC ማመልከቻ አስፈላጊ **አይደለም**።
  ከመጋቢ ንድፍዎ ውጪ በሆነ ትምህርት ቤት ቦታ ከተቀበሉ የዚያ መጋቢ ንድፍ መብት ሊያጡ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ እባክዎ ከትምህርት ቤትዎ ጋር ያረጋግጡ ወይም ወደ My School DC የስልክ መስመር በ (202) 888-6336 ይደውሉ።
- **DCPS ከአካባቢ ውጪ የሆኑ ትምህርት ቤቶች**፦ የMy School DC ማመልከቻ አስፈላጊ ነው።
- **DCPS የከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች**፦ የMy School DC ማመልከቻ አስፈላጊ ነው።
- **የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች**፦ የMy School DC ማመልከቻ አስፈላጊ ነው።

### ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከ 4-8 ክፍሎች) እያመለከቱ ነው? ከታች ያሉ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ያስቡ፦

- ተማሪዎችን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ከዚያ በላይ እንዴት ታዘጋጃላችሁ?
- በሁለተኛ ትምህርት ቤት የማመልከቻ ሂደት ውስጥ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለመርዳት ምን አይነት ሰራተኞች እና መርጃዎች አሉ?
- ምን አይነት ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ያሉ ተግባራትን፣ ልዩ ፕሮግራሞችን፣ እና የጉዞ እድሎች ይሰጣሉ?